# የዎያኔ አገዛዝ የወንጀል አፈጻጸም ዘዴ (ሞደስኦፐራንዴ)

ወያኔ መንግስት መሰል ታቋማት እና መዋቅር የዘረጋ እጅግ ኣደገኛ የሆነ ኢትዮጵያን ኣፈራርሰው የነርሱ ሊያደርጓት በሚመኙ ሃይሎች የተቀጠረ ቡድን ነዉ፤፤ወያኔ ባለሙያወችን ከሙያቸዉ ኢትዮጵያዊያንን ካገራቸዉ በመግፋት ኣገራችንን ለባዳን ኣሳልፎ የሰጠ ቡድን ነዉ፤፤ በመሆኑም ወያኔ ከባእዳን በሚሰጠዉ ኢትዮጵያን የማፍረስ ተልኮ የሚመራ በኢትዮጵያ ላይ የዘመተ ሃይል ነው፤፤ በዚህ መሰረት ወያኔ ህግን ወረቀት ላይ ኣስፍሮ በተግባር ወንጀል ይፈጽማል፤፤ ወያኔ ስለህግ ሲባል ከመስማት ዉጭ ጣእሙን ኣያዉቀዉም፤፤ የህግ የበላይነት እና የወያኔ ኣገዛዝ ኣጥፊና ጠፊ ናቸዉ፤፤

የህግ የበላይነት ማለትም ፥ በዚህ የሰለጠነ ዘመን እና የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት በሚከተሉ ዘመናዊ ኣገሮች፥ ባገሩቱ ዉስጥ ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮችን ለማስተዳደር ብቃት ያለዉ፤ሁሉም ሰዉ በህግ ፊት  እኩል የሆነበት፣ የህግ ስርዓት ያለበት ማለት ነው፤፤ "በህግ ፊት ሁሉም ሰዉ እኩል ነዉ" የሚለዉ የህግ መርህ ለወያኔ ባእድ ነዉ፤፤ ባ17 ዓመት የትግራይን ህዝብ ሲጨፈጭፍ፤ሲዘርፍና ባለቆቹ መመሪያ መሰረት ኢትዮጵያዊ የትግራይ ጀግኖችን ሲገል እና ትጥቅ ሲስፈታ ያካበተዉን ልምድ ወደ መሃል እና መላዉ ኢትዮጵያ ይዞ በመግባት ከጸረ ኣገር ቅጥረኛ ሽፍታ ወደ ቅጥረኛ መንግስትነት፤ሲለወጥ ለማስመሰል የሚጠቀምበት ባዶ ቃል ነዉ፤፤የህግ የበላይነት እዉን የሚሆነዉ የፖለቲካ መሪዎች በነጻነት የህግ ከለላ ተሰጧቸዉ እርይ ኣቸውን ሲያራምዱ፣ ነጋዴዎች በነጻ ገብያ ዉድድር ነግደዉ ጤናማ ትርፍ የሚያግኙበት : ማህበራዊ ፍትህ ተገቢውን የህግ ጥበቃ አጊንቶ ዜጎች በእኩልነት የሚታዩበት  ስርዓ-መንግስት ሲኖር ነው። ይህ ሲኖር ግልጽነት ና ተያቂነት ያለው የህግ አውጪ ተርጉአሚና አስፈጻሚ አካላት ይኖርራልኡ ማለት ነው። ወረቀት ላይ የሰፈረውን ህግ ባግባቡ የሚያስፈጽሙ የመንግስት ተቁአማት ክከሌሉ ህግ ብወረቀት ላይ የሰፈረ ተረት ተረት ነው።

ኢትዮጵያም ሆነች ሌሎች ዘመናዊ መንግስታት የህግ የበላይነት መርሆች ይቅበላሉ: ተቀብለውም ተቁአማትን ይገነባሉ መዋቅርም ይዝርጋሉ። በዚህም ህጋዊነትን ሽፋን ኣድርጎ የወያኔን  ተቁአማዊ አደረጃጀት ና መዋቅራዊ የወንጀል አፈጻጸም ዘዴውን ከዚህ ቀጥልን ዕናያለን።

ማንኛውም ዘመናዊ  መንግስት አገርን ከውጭ ጥቃትና  ከውስጥ ከሚነሳ የወንንጀል ድርጊት ለመከላከል የጸጥታ ተቁአማት የመጀመሪወቹ ናቸው። እነዚህ ተቁአማት በየትኛውም የህግ መመዘኛ : የየትኛውም የፖለቲካ :የእምነት ወይም የሃይማኖት: የጎሳ ቡድን ወገንተኛ መሆን የለባቸውም። ወገንተኝነታቸውም ለህግ ና ለህግ ብቻ ነው። ይህን አጠቃላይ ግንዛቤ ከያዝን በሁአላ ወያኔ ወንጀል ለመስራት እንዲያመቸው ተቅኡአማቶቹን ና አወቃቅራችውን እንዴት እንዳዋቀረ እናያለን።

1. ደህንነት : መከላከያ: እና ፖሊስ:- እነዚህ ተቋአማት መዋቅራቸው የተሞላው ለ 17 ዓመት የትግራይን ወጣቶች በጅምላ በመረሸን : የትግራይ አዛውንቶችን ኢትትዮጵያዊ ክብራቸውን በመግፈፍፍ: የትግራይ ጅግግኖችን ትጥቅ በማስፈታት: የኢትይኦጵያን የግዛት አንድነት ለመፈ ታተን ለተከፈተው ሰፊ ዘመቻ ታማኝነታቸውን ባስመሰከሩ ና ለ 23 ዓመታት በመንግስትትነት ስም ኢትዮጵያንን እያዋረዱ ባሉ ግለሰቦች ነው።እነ ዮሃነስ ኣንገታቸዉን የሰጡበትን፣ እነ ኣሉላ ክንዳቸዉን ያሳዩበትን የኢዮጲያ ኣካል ያስደፈረ የሃገር መከላከያ ሳይሆን የቅጥረኛዉ ወያኔ የግል ዘበኛ ሆኖኣል፤፤

2. የፍትህ ተቁአማት: የፍትህ ተቋአማት:- የሚባሉ ፍርድ ቤት ና አቃቢ ህግ ሲሆኑ በወያኔ አገዛዝ ጀግኖችን ለመወንጀል ፈሪወችን ለማስፈራራት: ህዝብን መሪ ለማሳጣት ወንጀለኞችን የህግ ሽፋን ለመስጠት: ተግተው የሚሰሩ ናቸው: በሃገራችን ከቤተክርስቲያን ና ከቤተ-መስጊድ ቀጥሎ ክብር የነብረው ፍርድ ቤት ዛሬ ረክክሶ የወያኔ ወንጀለኞች : የተውኔት መተወኛ አዳራሽ ሆኑአል።

3. የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ተቋአማዊ ና መዋቅራዊ : ወያንያዊ ወንጀል መሳሪያወች ናቸዉ። ወያኔወች የኢትይይኦጵያን ህዝብ በቡድን ሙብት ስም አቡአድነውና አስረው ለያንዳንዱድም ስም በመስጠት እነሱ ከፈቅዱላቸው ውጪ እንዳያስቡ በማድረግ ኢሃዴግ ና አጋር ፓርቲ በሚሉአቸው ተግተው በመስራት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ከፍተኛ የሆነ የማለያየት ስራ ይሰራሉ። በዚህም መሰረት ከውስጣችቸውም ሆን ከውጪ የፖለቲካ ፈተና ሲያጋጥማቸው አማራውንን ትምክተኛ : ኦሮሞውን ጠባብ: ትግራዩን ተንበርካኪ: ደቡቡን ጥቅመኛ: አጋር ፓርትወችን ጥገኛ በማለት በማሸማቀቅ እና የስነ ልቦና ጦርነት በተከታታይ ይፈጽማሉ፤፤ ከላይ በተጠቀስት ተቋማት በመጠቀም እያንዳዱ ኢትዮጵያዊ በነሱ ውስጥ ያለውም ሆነ ከነሱ ውጭ ስለ ኢትዮጵያዊ አመለካከት ና ብሄራዊ ራይ እንዳይኖረው ተግግተው እየሰሩ ነዉ።

4. ዲፕሎማቲች ተቋአማት፣ ላለፉት 23 አመታት የውጭ ጉዳይ ሚኒሥቴርን በመውረር ኢትዮጵያ በታሪኳ ገጥሟት የማያዉቅ የዲፕሎማቲክ ኪሳራ ባለማቀፍ መድረኮች ተከናንባለች: ሉአላዊነቷ ተድፍሩአል: ዳሩ ቀርቶ መሃሉ ዳር ሆኑአል። ኢትዮጵያችን መቀነቷን ፈትታ ገላዋን ለርኩሳን ገብያ ኣቅርባለች፤፤የወያኔ ተላላክኪወች ለኢትዮጵያ ጥቅምና ክብር ሳይሆን ለኢትዮጵያ ጠላቶች ጥቅም ሽንጣቸውን ገትረው ትከራከረዋል። ይህን በማድረግም ኢትዮጵያን የማፍረስና የማዋረድ ተልኩአቸውን በተቋማትና በመዋቅሮቻቸው ፖሊሲ ነድፈው ስትራተጂ ቀይስው እየተወጡት ናቸው።

አደረጃጀታቸውን ስንመለከተው የሚነግረን አንድ አደገንኛ የሆነ ጉዳይ አለ: እርሱም በኢትዮጵያ ውስጥ ተራ የግለሰቦች ዘረኝነት ብቻ ሳይሆን ተቋማዊ ና መዋቅራዊ ዘርረኝነት ውስጥ መግባታችንን ነው። የትናንቱን የደቡብ አፍሪካው አፓርታይድ የዛሬው የኢትዮጵያው ወያኔ መተካቱ ነዉ።ልዩነቱ ኣፓርታይዶች ላገራቸዉ ብልጽግና ሲሆን ወያኔወች ለቀጠሯቸዉ ባእድ ኣገሮች መሆኑ ነዉ፣

ዘርኝነትን በ ሶስት ደረጃ ከፍለው የሚከራከሩ የህብረተሰብ ሳይንስ ምሁራን አሉ ። አንደኛው በግለሰብ ደረጃ ያለ ዘረኝነት  ሲሆን ይህም ሌላውን ዝቅ አድርጎ የማየት: ማዋረድ: ማራከስ: የመሳሰልሉትን የሚያካትት ሲሆን: ሁለኛው ዘርረኝነት ይህንን ውርደት ና የበታችነት ተቀብሎ ከዚህ ጋር አብሮ የሚኖር ተስፋ ቢስ እና የተሸነፈ ህብረተሰብን የመፍጠር አዝማሚያ ያለው ነው። ሶስተኛው ተቋማዊ  ዘረኝነት የሚባለው ሲሆን ይህ ፖሊሲ ተነድፎለት  በፖለቲካ ኢኮኖሚና በአግገልግሎት ሰጪ ተቋአማት ፣መዋቅር ተዘርግቶለት አንድን ዘር ጠቅሞ ሌላውን ዘር የሚያቀጭጭ እና የሚያገል አደገኛ የሆነ የዘረኝኝነነት የመጨረሻ አስከፊ  ገጽታው ነው። በዚህ መሰረት የወኔን ተቋማት መዋቅራዊ ይዘትት ስንመለክት እጅግ በጣም  አሳፋሪ በሆነ ደረጃ  በአንድ ቡድን የተሞሉ ሆነው እናገኛቸዋለን። ለምሳሌ:- መከላከያ ሚኒስቴር : የደህንነት መስሪያ ቤት: ኢሚግሬሽን ባለስልጣን : የፌደራል ፖሊስ: የኢትዮጵያ አየር መንገድ: የትዮጵያ ቴሌ-ኮሙኒኬሽን: የመከላከያ ኢንዱስትሪ: ጉምሩክ: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትቲያን: ባንኮች እና ከሃገሪቱ ከ 50% በላይ የ ንግድ ተቋአማት መዋቅራቸው በተቋማዊ ዘረኝነት የተሞሉ ናቸው።

እነዚህ መስሪያ ቤቶች ለአንድ አገር ብኄራዊ ህልውና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና: እና ማህበራዊ ዋስትና ምን ማለት እንደሆኑ ለማንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ግልጽ ነው።

ይህን ካልኩ በሁአላ አገራችንን ለማዳን የትግልሉ አቅታጫ መሆን ያለበት ከላይ የተጠቀሱትን ተቋማዊ ዘረኝነትና አድሎ ለማስወገድ ትግሉ የህግ የበላይነትን ለማስከበር መሆን አለበት። የህግ የበላይነትን ለማስከበር ደግም ተቋማትና መዋቅሮቻቸው ሙያው በሚጠይቀው ብሄራዊ ሃላፊነትን ሊሸክከሙ በሚችሉ ዜጎች መያዝ አለብበት። ይህንም ለማየት ህግ አልባ የሆነውን ወያኔን በህጋዊና ኢትዮጵያዊ ሃይል መተካት ያስፈልግጋል። ለዚህም ትግሉ ከብዙ ፓርርቲወች ጋጋታ  : ከይሥሙላ ምርጫ : ከውሸት የነጻ ገባያ ማጭበርበሪያ፣ በፊት በዘረኝነት የጠመደና የተሳከረ የፖለቲካ ቅኘትን መስመር ማስያዝ የመጀመሪኢያው ስራ መሆን ኣለበት። የህግ የበላይይነትን የሚያስፍፈጽሙ ተቋማት ከተቋማዊ ዘረኝነት መዋቅር መጽዳት አለባቸው። ይህ በሌለበት እኩልነት የለም። እኩልነት በሌለበት ዲሞክራሲ የለም። አለም ከተባለ ፌዝ ነው:  እያፌዙ ደግሞ አገር መምራት አይቻልም። የሚፌዝበት የኢትትዮጵያ  ህዝብ በየአቅጣጫው ትግሉን ኣጠንክሮ መግፋት አለበት።

አበረ አዳሙ፣ ወርሃ ህዳር 2006 ዓ፣ም፣፣